የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No.73
ADDIS ABABA–3rd July 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፪/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የሱዳን ወደብ አጠቃቀም የፕሮቶኮል ስምምነት ማጽደቂያ
አዋጅ ........................................ ገጽ ፪ሺ፪፻፷፬

CONTENTS

Proclamation No. 352/2003
A Protocol Agreement on Port Sudan Utilization Ratification.
Proclamation ........................................ Page 2264

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፪/፲፱፻፺፭
### በኢትዮጵያና በሱዳን መንግሥታት መካከል የተደረገውን የሱዳን ወደብ አጠቃቀም የፕሮቶኮል ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የሱዳን ወደብ አጠቃቀም የፕሮቶኮል ስምምነት የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም ካርቱም ላይ የተፈረመ ስለሆነ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በሕግ– መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ “ የሱዳን ወደብ አጠቃቀም የፕሮቶኮል ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፪/፲፱፻፺፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም ካርቱም ላይ የተፈረመው የሱዳን ወደብ አጠቃቀም የፕሮቶኮል ስምምነት ፀድቋል።

### PROCLAMATION NO. 352/2003.
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE PROTOCOL AGEREEMENT ON PORT SUDAN UTILIZATION

WHEREAS, the Protocol Agreement on Port Sudan Utilization between the Government of the Fedral Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of the Sudan was signed in Khartoum on the 5th day of March, 2000;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratifed the said Agreement at its session on the 3rd day of July, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:-

1. *Short Title*
This proclamation may be cited as the " protocol Agreement on Port Sudan Utilization Ratification Proclamation No. 352/2003'.

2. *Ratification of the Agreement*
The Protocol Agreement on Port Sudan Utilization signed in Khartoum on th 5th day of March, 2000 is Ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· ስለ አስፈጻሚ አካል ሥልጣን

ይህ የፕሮቶኮል ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of Executive organ*

The Ministry of Trade and Industry is hereby empowered to implement this Protocol Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 3rd day of july,2003.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of July, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE